የሰፈው ሕዝብ ድምፅ

ለሰፊው ሕዝብ —ሠራተኛ፡ገበሬ፡ነጋዴ፡ወታደር፡ምሁር— መብትና
ጥቅም የሚታገል ጋዜጣ

የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ይቅደም::

ቁጥር 3 ቀን 28/12/66

ወዳጁና ጠላትን መለየት ያስፈልጋል

ስራ በተሰራ ቁጥር፡እንቅስቃሴ በተደረገ ቁጥር፡ያ ስራ ያ እንቅስቃሴ፡ማናቸውም ድርጊት በሌሎች ተመልካቾች ዘንድ መመዘኑ መተቸቱ አይቀርም:: እንደሁኔታው፡ከሰው ልጅ ፍላጐት ጋር እንደመሄዱ ወይም መለየቱ ምስጋናና ሙገሳ ወይንም ነቀፌታ ሊሰነዘርበት ይችላል:: ሰራን ሰርቶ፡ተግቢርን አከናውኖ ከትቸት ነፃ መሆን ጠርሶ አይቻልም:: ያለፈ ስራ ካለ፡መዘነ፡ካለ፡መረመረ፡ክፉና በጉው ተለይቶ ካለታወቀ አጥጋቢ ትምህርት መቅሰም፡መሻሻልና ወደፊት መራመድ አይቻልም:: ክፉም ሆነ በጉ፡ትምህርት የማይሰጥ ስራ ሊኖር ስለማይችል ስራንና ትቸትን ለመለያየት መሞከር ትልቅ ስህተት ነው፤ መሰረታዊውንና ተራማጁን የፍጥረትን ህግ መቃረን ነው::

ወደጊዜው ፍናና ብጠባጭ ሁኔታያቸ መለስ ብለን ስንመለከት በተለያዩ መግለጫያቸ ተደጋግሞ እንደታየው ደርጉ ትቸትን እንደጠር የሚፈራ ይመስላል:: ብዙ የሚሰሩ ጎገሮች እያሉ "አሉ ባልታን" ለመቧቃም ትልቅ ዘመቻ ያደርጋል:: "ነቀፌታን የማይቀበል መንግስት ዘለቄታ የለውም" የሚለውን ዘይቤ ተክክለኛነት ለማረጋገጥ ዛሬ ብዙ መሄድ አያስፈልገንም:: የነአክሊሉ ሃብተወልድ መንግስት በቂና ህያው ማስረጃ ነው:: ይህን ጠቀሊላው ሕዝብ በተለይም ጠሩ ጥሩ አድርጉ አይቶ ታል:: ታዲያ ዛሬውኑ ነቀፌታን እንዴት አድርገን እንፈራለን? በሕዝቡ ጠላቶቸ ላይ የመጀመሪያው ጭላ ገና ከማረፉ የነርሱን ውድቀተ መነሻ እንዴት እንዘነጋለን? ዛሬ በነቀፌታ ላይ እንቺህ ያለ ዘመቻ ለምን ይደረጋል? ገና ምኑ ተያዘና ምኑ ተሰራና ነቀፌታን ለመከላከል ይምከራል?

ነቀፌታን ከመቃወም በፊት ነቀፌታን ራሱን በመልክ በመልኩ መለየት ያስፈልጋል:: በወዳጅ፡በመንገድ ጊደኛ የሚሰነዘር አራማጅ ነቀፌታ አለ:: በጠላት የሚሰነዘርጉታችና የተንኮል ነቀፌታ አለ:: ወዳድና የመንገድ ጊደኛ የሚገኘው ወደአንድ ግብ በአንድ አቅጣጫ ለመሄድ ስንነሳ ነው:: በዚያ አቅጣጫ የሚጋዝ ሁሉ፡ወደዚያ ግብ የሚያመራ ሁሉ ለጊዜውም ቢሆን ወዳጅ ነው፤ እስከተወሰነ ርቀት እስከተወሰነ ደረጃ ድረስ ብቻ ቢሆንም የመንገድ ጊደኛ ነው:: በነዚህ የሚቀርበው አሰብ በሙሉ፡በነዚህ የሚቀርበው ትቸትና ነቀፌታ ሁሉ በመሰረቱ ጉዞውን ለማሰመር መንገዱን ለማቃናት ነው:: የመደብ ትግልን ያህል የተሰበጣጠረ፡የተወሳሰበና አስቸጋሪ ጉዳና የለም:: በገዥና በተገዥ መካከል ትግል በሚደረግበት ወቅት ትግሉን ለማፋፋም፡ለትግሉ ጥርት ያለ መልክ ለመስጠት፡መንገዱን ለማቃናት፡ዉቃኝ ገዥያቸን በሚገባ ደምስሶ ከጭቆና ነፃ ለመውጣት ሲባል የሚደረግ ነቀፌታ በሙሉ ከወዳጅ የመነጨ የማበረታቻ ነቀፌታ፡ገንቢ ነቀፌታ ነው:: በጉ እስካሰቡ ድረስ፡አሳማን እስካልቀየረ ድረስ ነቀፌታ እንደጠር የሚፈራበት ምንም ምክንያት ያለ አይመስለንም:: እርግጥ ከበጉ አሰብ የፈለቀ ነቀፌታ እንዳንዴ ስህተትን ያዘለ ሊሆን ይችላል:: ታዲያ ከወዳጅ መቅረቡ ከታወቀ ራሱ ነቀፌታው ተመልሶ ሊታረም የሚችል መሆኑ እንዴት ይዘነጋል? ይህን ያህል ሊያሸብር ሊያስቀጣ አይገባውም:: በመሰረቱ ከጠላት ከሚመነጭ አጥፊና አፍራሽ ነቀፌታ ይለያል:: ስህተት ኖረበት አልኖረበት አሳማው ወደፊት ለማራመድና ለመገንባት ነው እንጅ ለመጉተት፡እንቅፋት ለመሆን አይደለም::

ደርጉ እንዴት በአፍራሽና የተንኮል ነቀፌታና፡ከበጉ አሳብ በመነጨ ገንቢና ወደፊት አራማጅ ነቀፌታ መካከል ልዩነት ማውረግ ተሳነው? ለምንድነው ከሕዝብ ወገን በሚሰነዘሩትና ከጠላት በሚወረወሩት አስተያየቶችና ትችቶች መካከል ልዩነት የማያደርገው? ለምንድነው ሁሉንም 'አሉባልታ' እያለ የሚጠራው? መሰረት የሌለው በአወናባጆች የሚነዛው ፍሬከርስኪና ከሕዝብ ወገኖች፡ለሰፊው ሕዝብ መብትና ጥቅም፡በሕዝብ ስም የሚቀርበው ትችት እንዴት ባንድነት 'አሉባልታ' ይባላል? 'የመሰፍንትና የመኪንንት ቀሪቶች' የሚነዙት 'አሉባልታና' ከተራማጅ የሕዝብ ወገኖች የሚቀርቡት ጥርትና ግልጥ ያሉት ትችቶችና ጥያቄዎች ልዩነታቸው የሰማይና የምድር ያህል ነው፡፡ ደርጉ ሆን ብሎ ነው ወይስ ሳይታየው በመቀረቱ ነው ሁሉንም ባንድ የቀሽሽ መጣያ ቀርጫት ውስጥ የሚጥለው?

ተራማጅ የሕዝብ ወገኖች ደርጉን ምን ብለው ነው የተቹት፡ የነቀፉት? ያቀረቡበት ሂስ ምንድነው? ምን አደረግህ፡ምን አላደረግህም ነው ያሉት? የተወሰደው አርምጃ፡የተሰራው ስራ በቂ አይደለም ነው የተባለው፡፡ ጠቅላላና ዝርዝር ፕሮግራም ይውጣ፣ ጠቅላላ አቋም ይገለጥ፡ስራው ይጣደፍ፡ለውጡ በተከታይ መልክ ይያዝ፡ይስመር ነው የተባለው፡፡ የሚቀርበው ብዙው ነቀፌታ ማመንታት መጉተት ባዛ፣ ፈጠን እንበል፡ቁርጥ ያሉ አርምጃዎችን እንውሰድ፣ለውጥን ለሕዝቡ አምጭዎች ነን ብለን ራሳችንን መሰየማችን ቀርቶ የለውጡ መሪተ ሰፊው ሕዝብ መሆኑን እንመን፡እንቀበል፣ ከሕዝቡ ጋር ሆነን በአንድነት እንታገል፣ ሕዝቡ በለውጡ እንቅስቃሴ ውስጥ አትሳተፍ በመባል አይከለከል፣ የራሱ ነውና ነው የምንለው፡፡ ከዘውድ አገዛዝ ጋር የግድ የምንጠበቀበት ምክንያት የለም፣ ሰፊው ሕዝብ የተበዘበዘውና የተጨቆነው በዚሁ በዘውድ ስም ስለሆነ ለመጨረሻ ጊዜ እንሰናበተው፣ ንጉሱም መሳፍንቱም በውንብድና ቸውና ወንጀላቸው መሰረት ይታሰሩ፡ይቀጡ፡ከሕዝቡም የቀሙት ሃብት ለሕዝቡ ይመለስ ነው የተባለው፡፡

ደርጉ ባንድ ፊት ነፃነትን አመጣሁ እያለ በሌላ በኩል ዝም በሉ አትተንፍሱ አትሰብሰቡ አትሰለፉ ማለቱ ይቀር፣ ማስፈራራቱ መዛቱ ማሰሩ ይቁም፣ የታሰሩትም በቶሎ ይፈቱ፣ ደርጉ ይህንን ተቶ ከሕዝብ የተውጣጣ መንግስት ይቋቋም፡ጊዜአዊ መንግስት ይመስረተ ነው የተባለው፡፡ ታዲያ እነዚህንና የመሳሰሉትን ትኦክለኛ የሰፊው ሕዝብ ጥያቄዎች ማቀረብ 'አሉባልታ' ከጠላት የቀረበ አፍራሽ የተንኮል ፍላፃ ነውወይ? የኩንጉው ዘማች ጠር ጉዳይስ ቢሆን ይህን ያህል የሚያሸብር፡ይህን ያህል የሚያስቀጣ፡ይህን ያህል የስም ማጥፋት ዘመቻ የሚያሸው ነውወይ? ተክክለኛውን መፍትሄ ወደመሻቱ ብዙ የሚያራምድ አይመስለንም፡፡

ዛሬ ሕዝቡንም ጦሩንም የሚሰበስበው በጠላቶቻችን በመሳፍንትና በመኪንንት ላይ የሚደረገው ዘመቻ፡በነርሱ ላይ የሚወሰደው አርምጃ ነው፣ አገራችንን ከወደቀበት አዘቅት ውስጥ ለማውጣት የሚደረገው ተጋድሎ ነው፡፡ የሁላችንም የግል ጥቅም ዝና ወይም ስልጣን መሻት ከአገር ጉዳይ ጋር ከሰፊው ሕዝብ ጉዳይ ጋር ሲተያይ ቦታ የለውም፡፡ በዚህ አንፃር ማናችንም ብንሆን ከደርጉ ውስጥም ሆነ ከውጭ በርትተው የማይታገሉ፡እንዲያውም በአንቀፋተነት የሚገመቱ ሰዎች ካሉ ስማቸው ተጠቀሰም አልተጠቀሰ ካሉበት ቦታ፡ከተሰጣቸው ስራ ተነስተው በሌሎች በተሻሉ ሰዎች ቢተኩ እንዴት ይከፋናል? በሃቅና በእውነት ስለሰፊው ሕዝብ ብለን ከተነሳን ይህንን የማናደርግበት ምን በቂ ምክንያት ሊኖረን ይችላል? በጦዝቡ ፍላጐትና ጥያቄ መሰረት የማይሰሩ፡በተንኮል ወይም በቸሎታ ማነስ ስራው እንዳይጠደፍ ወደሃላ የሚጐተቱ በደርጉ ውስጥ አፍ ቋል ቶ የሉም ለማለት ይቻላል ወይ? ሆድ ሲያውቅ ደሮማታ እንዳይሆን፡፡ ዛሬ ገፊት በዝቶ፡ነገሩን አብዛኛው ሰው እውቀት ከመውጣቱ በፊት በየቀኑ የንጉሱን ወንጀል እንድ ባንድ በዜና ማሰራጫዎች መዘርዘር ቀርቶ ስሙን እንኳን በደርጉ ውስጥ ማንሳት የተከለከለ ነበር፡፡ ከሕዝብ መካከል የንጉሱን ወንጀልና ውንብድና ለማጋለጥ የጭቆናችንማ 'እነዚህን መረሽን ነው' የተባለበት ጊዜ እንደነበረ የሚታወስ ነው፡፡ ከበሬ አባሎች ዘንድ የኤርትራን ጉዳይ እንወያይበት የሚል አሳብ ሲቀርብ ወረቀቱ ተጨምድዶ ቀሽሽ መጣያ ቀርጫት ውስጥ የተጣለበት ጊዜ ነበር፡፡ ዛሬስ ምን ያህል ነው ለውጡ? ምን ያህል ነው መሻሻሉ? ደርጉ እነዚህን ጉድለቶቹን ጊዜው ከሚጠይቀው ስራ ጋር፡ከሕዝቡ ፍላጐት ጋር በደንብ አገናዝቦ በማረም ወደፊት ለመራመድ ዝግጁ ነውወይ?

በሰፊው ሕዝብና በደርጉ መካከል ያለው ግንኙነት ግልጥልጥ ያለ መሆን አለበት፤ ደርጉ ወደሕዝቡ መምጣት፡ልብ ለልብ መገናኘት አለበት ባዩቸ ነን:: ይሽንገንና የመሰሰሉትን ስንለ እኛም አቃማችንን በመደጋገም ግልጥልጥ ለማድረግ እንፈልጋለን:: በግለ ጥቅም የተነሳሳን አይደለንም:: ለራስ ብቻ የሚሉትን አድርባይ ስግብግብ ግለኖቹ እናወግዛለን እንቃወማለን:: ለዚሁም ሰለጠን ሹመት የምንሻ ሰዎች አይደለንም:: የውስጥ አድሃሪዎቹ ሆነ የውጭ ጠላቶቹ መሳሪያ አይደለንም:: ለኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ መብትና ጥቅም፡የኑሮ መሻሻል፡ና ብልጽግና፡ወደፊት እርምጃና ልማት ህይወታችንን በመሰዋት ጭምር እስከመጨረሻው እንታገላለን:: ይህ ነው አላማችን፤ ይህ ነው ዋናው አቋማችን:: የመጨረሻውም ድል የሰፊው ሕዝብ፡የሰፍ ቶአደረ የወዝአደረ መሆኑን ሁሉም አጥርቶ እንዲያውቅልን እንሻለን::

ከዚህ በፊት በተራማጅ የሕዝብ ወገን ሃይሎች በልዩ ልዩ ጽሁፎች እንደተገለጠው ደርጉ የሰፊውን ሕዝብ መብትና ጥቅም ለመጠበቅ በሚያደርገው ተጋድሎ፡በሚወስዳቸው ሕዝቢዊ እርምጃዎች የተራማጅ ሃይሎችን ድጋፍ ያገኛል:: የሕዝብንም ድጋፍ ይቀዳጃል:: ይህ የማያጠራጥር ነው:: የሰፊውን ሕዝብ ጥያቄና ፍላጐት ተከትሎ እስከሰራ ድረስ በደርጉ ላይ የሚመጣውን ጠላት ከሰፊው ሕዝብ ጋር ሆነን እንደምንመክትና ድምጥማጡን እንደምናጠፋው ከጥርጣሬ ውስጥ የሚገባ አይደለም:: ስለሆነም ከደርጉ ጋር አንድነት ለመሄድ የሚቻለው የሰፊውን ሕዝብ መብትና ጥቅም ለመጠበቅና ለማስከበር የሰፊውን ሕዝብ ፍላጐት ተከትሎ እስከሚሰራበት ድረስ ነው::

ደርጉ ብዙ ጊዜ አቋሙን ግልጥልጥ አድርጉ አንዲገልጽና ጠቅላላና ዝርዝር ፕሮግራሙንም አንዲያወጣ ከሕዝብ ወገን በመደጋገም ቢጠየቅም እስካሁን ድረስ ካንዳንድ ነጠላ ድርጊቶቹ በስተቀር ምንም ያደረገው ነገር የለም:: ይህ መቼም በጣም ግራ የሚያጋባ ነው:: እነዚህ በቁጥ ቁጥና በተናጠለ መልክ የሚወሰዱት እርምጃዎች ዋጋ የላቸውም ለማለት·አይደለም፤ አላቸው:: በተለይ በዋናው የኢትዮጵያ ሕዝብ አቀርቋዞ በአጼ ሃይለስላሴ ላይ ሰውኑን የተወሰደው የማጋለጥ ዘመቻ ለሕዝቡ ትልቅ ትምህርት የሚሰጥና ድጋፍም የሚያስገኝ ነው:: ግን በዚህም በኩል ፈጠን ማለትና ወንጀለኖቹን ከነግብርአበሮቹ ወደሕዝቢዊ የፍርድ ሸንጐ ማቅረብና ጊዜያዊ መንግስት ማቀም ያስፈልጋል:: በዚህ ጋዜጣ ባለፈው እትም ላይ የወጡትንም ሕዝቢዊ ጥያቄዎች በስራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ ያስፈልጋል:: በዚህ በኩል ማመንታቱ ለጠላት እንጅ ለሰፊው ሕዝብ የማይጠቅምና የማያመቸ መሆኑ ግልጽ ነው::

በሌላ በኩል ሰፊው ሕዝብ ሁሉንም ነገር ደርጉ ላይ መጣልና ለደርጉ መተው የለበትም እንላለን::በየመስሪያ ቤቱ በየሰፈረ በየአድረ በየማህበረ በያለበት መገናኘት መወያየት መደራጀት፡አድሉን በእጁ ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል:: የጦር ሃይሎች ደርግ ሁሉን ነገር ያደርግልኛል መሬት ይሰጠኛል፡ስራ ይሰጠኛል ፍትህና ርትእ ያመጣልኛል ብሎ አንጋጠ መጠበቅ የለበትም:: ሰፊው ሕዝብ አድሉን በገዛ እጁ ውስጥ ለማስገባት ቀርጠ መነሳት አለበት፤ መደራጀት አለበት:: መደራጀት መደራጀት መደራጀት ያስፈልጋል:: መብቱን ለማስከበር ጥቅሙን ለማስጠበቅ የሚችለው በመደራጀትና በቁራጥነት በመታገል ብቻ ነው:: ከሰራተኛው ከገበሬው ከዝቅተኛው ነጋዴ ከዝቅተኛው የመንግስት ሰራተኛ ከገበሬውና ከባለእጁ፡እንዲሁም በልዩ ልዩ ሙያ ከተሰማሩ ጠቢባን፡ከመምህራን፡ከተማሪዎች፡ከተራ ወታደርና ከባለሌላ ማእረጉች፡ከተራማጅ ምሁራን፡ከሰራአጦች ወዘተ. የተውጣጣ <u>የሰፊው ሕዝብ ትግል አስተባባሪ ደርግ</u> ቶሎ ብሎ ማቋቋም የሚያስፈልግ ይመስለናል:: ይህ በአሁኑ ጊዜ በጣም አስፈላጊ ነው:: ይህን ካላደረገን ምንም ያህል ዋስትና የለንም:: አጥብቀን እንድናስብበት ያስፈልጋል::

የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ያሸንፋል፤
አድሃሪዎችና ወደሃላ ጉታቾች ይወድጣሉ::



የሚወዱትና (?) የሚወዳቸው ሕዝባቸው የሚቀምሰው ሥርፋሬ አጥቶ በረሀብ አለንጋ እየተጠበሰ ፣ ለሠሯቸውና ለችግሩ እንኳንስ እርዳታ ሊያደርግለት ይቅርና መራቡም ፣ ግለቁም እንዳይታወቅ ተሸርጉ ከአንድ ሙቀ ቢህ ሕዝብ በላይ እንደዚህ ሆኖ ሲያልቅ ውሾቻቸው እንደሚታየው እየተቀላሙ ይቀለባሉ ። ኧረ ለገቱ ጉድ ተነግሮ !

ከሰው ይልቅ ለውሻ?

የታረዘው የተራበው በለጆሙ ብቻ የቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላቶቹን የመበቀያው ጊዜ ተዳርሷል። ከሁሉ አስቀድሞ የሕዝቡ ጠንቅ የብዝበዛው መሃንዲስ የሆኑትን አጤ ሃይለስላሴንና ንጉሣውያን ቤተሰብን ከነግብርአበሮቻቸው ከፍርድ ሸንጉ ገትሮ በማያዳግም ሁኔታ መበቀል ይኖርበታል። በረሃብ አለንጋ እየተገረፈ እንደቅጠል የረገፈው፣በልዩ ልዩ ደዌ ያለ እድሜው የተቀጨው፣ በድንቁርና ቁርበት በቁመናው የተገነዘው፣ ሃፍረተስጋውን የሚሸፍንበት የሌለው ወዝአደር፣አርሶበሌው፣ስራአጡ ወዘተ. እውነተኛ ጠላት ሃይለስላሴ ስለሆኑ ያለአንዳች ምህረት ሊፋረዳ ይገባል። የበሰበሰውንና ጊዜው ያለፈበት የአስተዳደር ስርአት የበላይ ጠባቂና ፈላጭ ቀራጭ በመሆናቸው ብቻ አይደለም ሕዝቡ የሚዳኛቸው።

ሃይለስላሴ ለይስሙላ ' የምንወደውና ሁልጊዜ የምናስብለት ሕዝባችን ' እያሉ የሚያታልሉ ትንና የሚያደነዝዙትን ሕዝብ ከሰው አይቀጥሩትም ፤ ፈጽመው ይንቁታል ፤ ይጠሉታልም ። ከኢትዮጵያ ሕዝብ ይልቅ ውሾችንና የጫር አራዊትን እንደሚያከብሩና እንደሚያፈቅሩ ብዙ ማስረጃዎች አሉ ። ሰፊው ሕዝብ የአለት ጉርሱን አጥቶ በችጋር እያለቀ እሳቸው በቤተመንግስታቸው የሚገኙትን ውሾች የጫር አራዊትና ሌሎች እንስሶች ጣፋጭ ምግብና ምርጥ ምርጥ ስጋ ሥመግባሉ ።

ኢትዮጵያ በጣም ወደሃላ ከቀረተና ምስኪን ተጽዋች ከሆኑት አገሮች አንዷ ሀና ሰለ እጩ ቡየሄጹበት ሁሉ ወርቀ ይቸራሉ ፤ ብር ተሸክመው አለምን በመዘር ይመፀደቃሉ ። ሕዝቡ በችግር አለንጋ ሲገረፍ ከስጩስት ሙሰዬን ብር በላይ አውጥተው የአፍሪቃ አጻራሽን አሰሩ ፤ በካሊፍር ኒያ ለሜገኝ አንድ ዩኒቨርሲቲ ከመቶ ሺ ብር በላይ ለገሱ ፤ ለአቁጣቶቻቸው እስከ 40 ሺ ብር ለሽተ መግዣ አያሉ ይሸልማሉ ። ለውጭ አገር እንግደች ማስተናገጃ አየተባለ በየጊዜው የሚፈሰሰውን ብር መጠን ለመገመት ፈጽሞ ያጻግታል ። የሕዝቡን ንብረት ከመሰፍኖቻቸውና ከመኩንኖቻቸው ጋር ይቃረጡታል ። አብዛኛው ለምና ምርጥ መሬት /ከለምለሙ መሬት 46.6 በመቶ የሚሆነው/ የተያዘው በእርሳቸው ፡ በውላጆቻቸው በአገሰጋዬቻቸውና በከፍተኛ ባለስልጣኖች ነው ። አንበሳ አውቶቡስ ፡ መብራት ሃይል ፡ በጉ አድራጉት ፡ ቢራ ፋብሪካ ወዘተ . በመሳሰሉት ኩባንያ ዎች ውስጥ በግልና በልዩ ልዩ ስም ብዙ ሃብት ከማከማቸታቸውም ሌላ የመንግስቱን ንብረት እንደግል ሃብታቸው ይጠቀሙበታል ። ሽረ ስንቱ ተዘርዝሮ ያልቃል ። በአጠቃላይ ኢትዮጵያ የሃይለስላሴና የግብረአበሮቻቸው የግል ንብረት ናት ቢባል ከእውነት የራቀ አይሆንም ።

ሃይለስላሴ ታይታን የሚወዱ በዝባዝንኬ እንደህፃን ልጅ የሚደሉሉና እንደአምላክ ሲመለክ ቧቸው የሚደሰቱ ከንቱ ሰው ናቸው ። በራሳቸው የማይተማመኑ ለይስሙላ የሚኖሩ ምስኪን ፍጡር ናቸው ። አገርወዳድን በሙሉ የሚያንገፈግፈውና የሚዘገንነው ይህ ጠባያቸውና አሰፋሪ ድርጊታቸው ብቻ አይደለም ። ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነትና ክብር ከጠላት ጋር በመዋጋት ደማቸውን ለአፈሰሱት አጥንታቸውን ለከሰከሱት አርበኖች ሃይለስላሴ መታሰቢያ ሃውልት ሲያሰሩ ፤ ሉሉ ለተባለው ' ተወዳጅና አኻቢ ' ውሻቸው ሃውልት አሰርተውለታል ። እስቲ ' በትልቁ አስተዛዘኖቸው ' በሉሉ ሃውልት ላይ የተቀረፀውን ፡ በጀርመን ጋዜጣ ላይ ታትሞ የወጣውን ጽሁፍ እንመልከት ፡ ፡ ' . . . ግርማዊ ንጉሰ ነገስት በአፍሪቃ ፡ በአውሮፓና በአስያ አንጎሁም በሰሜንና በደቡብ አሜሪካ ባደረጉት የወዳጅ አገሮች ጉብኝት ሉሉ በመከተል ያለተለይ ታማኝ አገልጋይ እንስሳ ነው ። ሉሉ በሚያዝያ 27 ቀን 52 ዓም አጂስአበባ ተወለዳ ፤ በሃምሌ 16 ቀን 61 ዓም ሞተ . . . '

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ ! እንግዲህ ለመዋረዳችን ፡ ለመረገጣችን ፡ ሰባዊ መብታችንን በጨካኙ ፀለጠ ሃይለስላሴ ለመገፈፋችን ከዚህ የበለጠ ምን ምስክር አለ ? እረ እስከመቼ ድረስ ነው እኚህን መሃይምና አረመኔ ንጉስ ' ያንድነታችን ምልክት ናቸው ' እያልን ራሳችንን አዋርደን የምንሸከማቸው ? እረ እስከመቼ ከውሾች በታች ሁነን በሃይለስላሴና በንጉሳውያን ቤተሰብ እያመለክን ተረግጠን እንገዛ ? እረ እስከመቼ ነው በአለም ሕዝቦች እንደተናቀን እንደመፀወትን የምንኖረው ? አሪያና ፋላች እንደጫሉት ሃይለስላሴ ውሾች ባጠገባቸው አዘውትረው እንዲገኙ የሚፈልጉት ወዳጆቻቸውንና ጠላቶቻቸውን ለይተው ሊነግረለቸው ይችላሉ በሚል የጥንቃላ እምነት ነው ይላላል ። እረ በጥንቃላ ስንቶቹን ንፁሃን ኢትዮጵያውያን አበላሽተው አሰበረው አስገድለው ይሆን ? የሃይለስላሴ በደልና ግፍ በዚህ ብቻ አያልቀም ። ፋሽስት ኢጣልያ ኢትዮጵያን በወረራት ጊዜ አርበኞቹን አደራጅተው ጠላትን በግንባር ቀደምትነት መቃቃም ሲገቢቸው የሕዝቡን ወርቀና ያለ የሌለውን ገንዘብ አሟጥጠው ወደአውሮፓ ፈረጠጡ ። ኢትዮጵያም የእንግሊዝ ቀኝ ግዛት እንድትሆን ጠየቁ ። የእንግሊዝ መንግስት ግን ከኢጣልያ መንግስት ጋር በጥቅም ለመጋጨት ስላልፈለገ የሃይለስላሴን ጥሪ አልተቀበለም ። ማርቀስ መንክር እንደጨሉት ሃይለስላሴ በስደት ጊዜያቸው እንኪን የንግድ ስራቸውን አላቋረጡም ነበር ፤ በኢየሩሳሌም የጫገኙን የኢትዮጵያን ገዳም ለመሸጥ ቃክረው ነበር ።

ወደኢትዮጵያም በተመለሱ ጊዜ ባገር ፍቅር ተመስጠው ተልቀ መስዋእት ለተቀበሉት አርበ
ኖች ተገቢ የጋ ቸውን በመክፈል ፈንታ አንዲያውም አለፈው ተርፈው በህይወታቸው ያገኙአ ቸውን አጠ
ፋለ ቸው አሳስረ አ ቸው አስጋዙአ ቸው:: አርበኖችንም የጭመስመስ የስደተኛ ቡድን አ ቋቋሙ:: የስደ
ተኛ ቡድን አባሎችም ኢትዮጵያን ለጠላት አሳልፈው የሸጡ ባንደች:ባገርወዳደች የደም ጉርፍ የታ
ጠቡ:ከንጉሱ ጋርአብረው የፈረጠጡና ሃይለስላሴን አንደጣአት የሚያመልኩ ሀሲናቢሶች ና ቸው::
ለዚሁም በሃይለስላሴ መንግስት በአገርወዳጅነታቸው ብቻ ተወንጅለው በአስር ቤት የማቀቁትንና
የተጉሳቆሉትን አ ነአለቃ ፈጠነ:አ ነመ ቶ አለቃ በቀለ አናሲሞስ:አ ነአ ቶ ነገደ ገብረአብ:አ ነአፈን
ጉስ ገብረመድህን ወዘተ. የሚናገሩትን ማሰታወስ ብቻ ይበቃል::

ሃይለስላሴ የሰው ሬሳ በመኪና የሚያስጉተ ቱ፣ ሬሳ በአደባባይ የሚያሰቅሉ የሰው ልጅ
ጠር ና ቸው:: የታህሳሳውያን ደም በከንቱ ያፈሰሱ፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ በረሃብና በጥም አለንጋ
አስገርፈው ሬሳውን ለጌር አራዊት ያበሉ፣ ሕዝቡ በረሃብ መቀሰፍት ሰመ ታ ለውሽ ቻቸውና ለአውሬያ
ቻቸው ምርጥ ስጋ የሚቀልቡ፣የሰው ልጅ ሬሳ በየጫረ ሲቀር ለውሻ ቸው ሃውልት የሚያሰሩ ጉበዝ
ና ቸው::

የሃይለስላሴ ግብረአበሮች በወሎ ሕዝብ ጉዳይ ተጠያቂ መሆና ቸው ትክክል ነው:: መራራ
ጽዋ ቸውን ፊት የሚሉበት ጊዜ ተቃርቧል:: ሆኖም ለዚህ ሁሉ በመጀመሪያ ደረጃ ተጠዘቅ መጠየቅ
ያለባ ቸው ሃይለስላሴ ና ቸው:: አለበለዚያ 'አህያውን ፈርተ ዳውላውን' አንደተባለው ይሆናል::
ምክንያቱም አሳ ቸው ሳያውቁት የሚሰራ ነገር የለምና ነው::

የመርማሪው ኮሚስዩን በወሎ ሕዝብ ላይ በደረሰው የረሃብ መቀሰፍት በሃላፊነት የሚጠየቁ
ትን ከፍተኛ ባለስልጣኖች ለሕዝብ ባስታወቀ ጊዜ የጠቅ[illegible]ግዛቱ አንደራሴ ቸግሬን ለንጉሱ
ጭምር ማስታወቃ ቸውን ገልጠአል:: ታዲያ ንጉሱ[illegible]ደርሳ ቸው ምን አርምኛ ወሰዱ? የኢት
ዮጵያ ሕዝብ በሰሜን በደቡብ በምስራቅ በምእራብ ከቸገር ሲረገፍ ላፍሪቃ አንድነት በአለ:ለለደት
በአለ:ለንግስ በአለ:ለሽሽት መልስ በአልና በጠቅላላው ለከንቱ ውዳሴ የሕዝብ ገንዘብ አንዲፈስና
አንጂረጭ ሲያደርጉ የጠዘቡን አልቂት አስታውሰውታል?

የውጭ ጋዜጠኖችና ደራሲያች የሰ ቸውን ትልቅነትና ገናናነት'ለአለም ሕዝብ አንዲያስታውቁ
'የበላም ሸልማትን' አንዲያገኙ የሃሰት ሙሪሞባ አንዲነፉላ ቸው ሲያባብሉ ስለወሎ ጉዳይ ስለሕዝቡ
እልቂት ያነሳውን ኢትዮጵያዊ ሁሉ አንዲታሰረ አንዲጉሳቆሉ አንዲረሽኑ አድርገዋል::'አሳ ቸው
የሕዝቡን ቸገር አያውቁም:አልሰሙም:አጥፊዎቹ ከስር ያሉት ና ቸው'አያሉ በማስወራት ሕዝቡን አስ
ክመ ቹ ለማታለል ይቻላል?

ከላይ እንዳመለከትነው የመርማሪው ኮሚስዩን የወሎን ጉዳይና ተጠያቂ ሊሆኑ የሚቸሉትንም
ባለስልጣኖች ስም ሲያስታውቅ እጠ ከዚያን ጊዜው የወሎ አንደራሴ በሃምሌ 27 ቀን 62 ዓም
የተፃፈ ደብዳቤ ከማግኘታቸው በቀር ስለሃላፊነታቸው ምንም ትቸት አልሰጠም:: ጠቅላይ ሚኒስትሩ
ከነሚኒስትሮቹ ወንጀለኛ ሆኖ ከተገኘ የበሰበሰው የአስተዳደር ስርአት ምሰሶ እንዴት በሃላፊነት
አንደማይጠየቁ አይገባንም:: በኛ አስተያየት በመጀመሪያ ደረጃ ተጠያቂው ሃይለስላሴ ና ቸው::
የመርማሪው ኮሚስዩን የተጣለበት ሃላፊነት ከባድ ስለሆነ ሽንጡን ገትሮ መስራትና ትክክለኛውን
ነገር ማቀረብ አለበት እንጅ ተጽእኖ ኖረበትም አልኖረበት አንዳንድ ጥፋተኞችን ሊያልፋ ቸው
አይገባም:: አንድ ቀን ራሱንም በሃላፊነት ያስጠይቀዋልና::

የኢትዮጵያ ሕዝብ በረሃብ እያለንጋ እየተገረፈ:በውሃ ጥም ጉሮሮው እየተሰጣተረ:በበሽታ
ሲጣቀቅ በሕዝብ ገንዘብ አለምን ከነውሽ ቻቸው የሚዘረትና የውሻ ሃውልት የሚያሰሩት አጠ ሃይለ
ስላሴ ተይዘው ለፍርድ ይቀረቡ::

የመሰፍንተ አገዛዝ ከገራቸን ይጥፋ፣
ትክክለኛው የሰፊው ሕዝብ ትግል ይቀጥላል::